ምንም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፉት መልእክቶች በተወሰነ ዘመን ለተወሰኑ አንባብያን የተወሰነ ጉዳይ [ትክክል ያልሆነ ትምህርትን ለማረም፣ ለማበረታታት፣ወይም ለመገሰጽ] አስመልክቶ የተጻፈ ቢሆንም ዛሬ በዘመናችን፣ ለምንገኝበት ሁኔታ፣ በፊታችን ላሉ ገጠመኞች ሁሉ የሚመጥን፣ የሚገባና የሚያስፈልግ ትዕዛዝ፣ ትምህርት፣ ምክርና ተግሳጽ ያዘሉ መልእክቶች እንደሆኑ እርግጥ ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር የአባታችን እና የአምላካችን ቃል ህያውና ዘላለማዊ ስለሆነ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ዘወትር ማንበብ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማካሄድ የሚያስፈልገን እነዚህን መልእክቶች በሚገባ ተረድተን መንፈሳዊ እምነታችንና ሕይወታችንን በዚሁ ረገድ እያነጽን ጌታችንን ወደ መምሰል የምንደርሰው በዚሁ ሁኔታ ስለሆነ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቆላስያስ የላከውን መልእክት በማጠናበት ጊዜ፤ በኛ ዘመን፣ በ2009 (Eth Calendar) በሕይወት ቢኖር ኖሮ ይህንኑ መልእክት ወደ ኢትዮጵያኖች በተለይም ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች የሚልከው መልእክት እንደሆነ በጣም አምናለሁኝ። ይህንን ለማለት የቻልኩበት ምክንያት ከዚህ በታች ከማቀርበው ትንታኔ በግልጽ ለመመልከት ይቻላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ የቆላስያስ ቤተ ክርስቲያንን ምዕመናን በወሬ እንጂ በአካል አያውቃቸውም። ከመሠረታቸው ወይም ከኅበኛቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል አይደሉም። በሮም በእስር እያለ በ60ዎቹ ዓመተ ምህረት ገደማ በኤጳፍራስ አማካኝነት ከደረሰው መረጃ ተነስቶ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እየተስፋፋ ያለውን የስህተት ትምህርት በመቃወም የቆላስያስ አማኞች ወደ እወነቱ፣ ወደ ክስርቶስ ወንጌል በአፋጣኝ እንዲመለሱ ያደረገውን/የሚያደርገውን መጋደል የሚያመለክት ጽሑፍ እንደሆነ ከምንባቡ መረዳት ይቻላል። ይህንንም በማስረገጥ በመልእክቱ ምዕራፍ 2 ቁጥር 8 ላይ "እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ። " በማለት ያስጠነቅቃቸዋል። ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው እየተስፋፋ የነበረው ትምህርት፤

1ኛ. ክርስቶስ ያስተማረው እና ሐዋርያት ያሰራጩት ወንጌል እንዳልነበረ እና የስህተት ትምህርት እንደነበረ፣ 2ኛ. መሠረት በሌለው፣ ሥረ መሠረቱ ከክርስቶስ ጋር ያልተያያዘ ሰዎች እንደራሳቸው ፈቃድ የመሠረቱት ወግ/ባህል (Tradition) እንደነበረ በተለይም በአይሁድ ባህል እና ሕግ ተጽዕኖ ላይ የተመሠረቱ ትዕዛዛት እንደነበሩ፣ 3ኛ. ከፍልስፍና ጋር (በተለይም በወቅቱ አንሰራፍቶ ከነበረው ከግሪክ ፍልስፍና ጋር) የሚመሳሰል አመለካከት እና እምነት እንደነበረ፣ እና 4ኛ. የሰውን እውቀትና አስተሳሰብ የሚማርክ እንደነበረ ለመረዳት እንችላለን።

የክርስቶስ ወንጌል ጌታ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ከኢየሩሳሌም ወደ ሰማርያና ሌሎች ከተሞች በተሰራጨበት ጊዜ እና ከአይሁዳውያን ወደ አሕዛብ በደረሰበት ጊዜ በአንድ በኩል የአይሁድ የሕግ ተጽዕኖ [ግርዘት፣ የምግብ ሥርዓት ወዘተ] በሌላ በኩል ደግሞ የአሕዛብ የፍልስፍና እምነት እየተቀየጠ ንጹሑን የወንጌል መልእክት የማደፍረስ ችግር እንደፈጠረ በርካታዎቹን የሐዋርያው ጳውሎስን መልእክት በምናነብበት ጊዜ እንመለከታለን። ከነዚህም የፍልስፍና ትምህርቶች መካከል ግኖስቲክስ በተሰኙ ወገኖች ይረጭ የነበረው የስህተት ትምህርት ዋነኛው እንደሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎችና ተመራማሪዎች ይገልጻሉ። የግኖስቲክስ ትምህርቶች ላይ ላያቸው የክርስቶስን የወንጌል ትምህርት የሚመስሉ ይዘቶች የነበሩቸው ሲሆን ውስጣቸው ግን መናፍቃዊ ነበሩ። በትክክል "የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች" አሊያም "ስንዴ የሚመስሉ እንክርዳዶች" ያስብላል።

እነዚህ ፈላስፋዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እየጠሩ (እያስመሰሉ) ካስተማርዋቸው ትምህርቶች መካከል፤ ክርስቶስ ከሰማይ የወረደ ቢሆንም በሥጋ አልተገለጠም (መንፈስ ነበረ)፣ ክርስቶስ መለኮት አይደለም፣ ለመዳን የተለያዩ የሰማያዊ ምሥጢራት (secret knowledge) እውቀት አስፈላጊ እንደሆነ [ስማቸውንም ግኖሲስ ወይም እውቀት ከሚለው የግሪክ ቃል ነው ያገኙት] እና በመጨረሻም የመላእክት ሥርዓትን በሚመለከትና የመላእክት ክብር/አምልኮ እና አማላጅነትን እንዳስተማሩ ይታወቃል።

ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህ እየተሰራጩ ስላሉት የስህተት ትምህርቶች እና የአይሁድ ተጽዕኖ በሰማበት ጊዜ ለቆላስያስ ክርስቲያኖች የላከውን መልእክት [ዛሬ ለኢትዮጵያውን ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች የሚያስፈልገውን መልዕክት] በዚህ መንደርደሪያ መነጽር አማካኝነት በሚቀጥሉት ጽሑፎች እንዳስሳለን።